# ኢትዮጵያችን

*የአንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 4 ቁጥር 5 ግንቦት ፪ ቀን ፪ ሺህ ፲፪ ዓ.ም.


## እስቲ ዝም እንበል

*የድምጽ ቅጂውን ለማድመጥ እዚህ ይጫኑ* (https://www.youtube.com/watch?v=wxm5ka610CE )

ዓለምን የቁም እስረኛ ያደረገው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ሀገራችን ላይ የፈጠረው ስጋት ከጊዜ ወደ ጊዜ አሳሳቢ ሁኗል። በትንሹ ለግማሽ ምእተ ዓመት ሕይወትን ከድህነት እና በሽታ ጋር አቆራኝቶ የኖረው ሕዝባችን ሲያስቡት ሚዘገንን መቅሰፍት ተደቅኖበታል። “ሞትን ተሸክመን እንዞራለን” ሚባለው ዛሬ የተገላቢጦሽ ሞት ተሸክሞን ሊዞር ይመስላል። ማንን ቅድሚያ እንደሚሸከም፣ የት እንደሚጥለን፣ ማንን ቅድሚያ እንደሚጥል፣ መተንበይ ባንችልም ብቻ ሁላችንም ዘንድ መጥቶብናል። ይህን አስከፊ ወረርሽኝ እምነት ላለን መከላከያው ጸሎት መሆኑን ብንገነዘብም እንዲህ በቀላሉ ለመቆጣጠር አዳጋች ይመስላል። በአለፉት ሁለት ወራት የተቀራረበውን ዓለም አይደለም ጎረቤት አራርቋል። ታማሚና አስታማሚን፣ ሟችና ቀባሪን፣ ተማሪና አስተማሪን፣ ነጋዴና ሸማችን፣ ሥራና ሠራተኛን ለያይቷል። ወረርሽኙ የተበገረው ወሬን ከጆሯችን መለየቱ ላይ ነው። እጅግ የከፋ አደጋ መሆኑን ተገንዝበን በማኅበራዊ ህይወት የሚያስከትለውን ምስቅልቅል ተረድተን፣ በኢኮኖሚው እያደረሰና ገና የሚያደርሰውን ውድቀት ተገንዝበን በፖለቲካው አልተንበረከክንም ባይ ቀቢጸ ተስፋ ቋጣሪዎች ባንሆን ይመረጣል።

ከኮረና ቫይረስ ወረራ በማስከተል ሰሞኑን በሀገራችን በመንግሥትና በአንዳንድ ተፎካካሪ የፖለቲካ ድርጅቶች የሚካሄደውን አሳዛኝና አሳፋሪ ውዝግብ እየታዘብን ነው። እውነት ለሀገር፣ ለሕዝብ ተቆርቋሪና አሳቢ ከሆንን ዛሬ ሕዝባችን ምን ላይ ነው ያለው? ዋናው ትኩረታችን ምን ላይ መሆን ይገባዋል? ብለን እራሳችንን የምንጠይቅበት ወቅት ላይ ነን። የሰለጠኑት ሀገራት ከአቅማቸው በላይ የሆነውን ይህን ወረርሽኝ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስና ለመከላከል ያለ የሌለ ኃይላቸውንና ትኩረታቸውን ቢያደርጉ ከአቅምና ችሎታቸው በላይ እንደሆነ እየተገነዘብን ነን። ወደ ኢትዮጵያችን ስንመጣ በሚልዮን የሚቆጠር እደጅ/ጎዳና አዳሪዎችን በየቤታችሁ ግቡ፣ ተከተቱ ስንል አለማፈራችን ይደንቀናል። ሌላው ቀርቶ በየቦታው የሚካሄደው ማፈናቀል በዚህ አስከፊ ወቅት እንኳ ጋብ ሲል አይስተዋልምና። በየአካባቢው ያሉ ግጭቶች ወረርሽኙን ሊያደምጡ አልፈለጉም። ወረርሽኙ መንግሥት ላይ ብቻ የመጣ የመሰላቸው አቋራጭ ፈላጊዎች ሕዝባችንን ዘንግተዋል። ወረርሽኙ ሕዝብ ቢጨርስ፣ ሀገር ቢያዳክም ደንታ የሌላቸው የባዕዳን ቅጥረኞች ግርግር ለእነሱ አመች መስሏቸው ፉከራ ይዘዋል። ገና ሲጀመር የህወሓት/ኢሕአዴግን ሕገ መንግሥት አስፈጻሚ ነኝ ያለው “ለውጥ አራማጅ” መንግሥት ዛሬም “ሕገ መንግሥት ወይም እርምጃ” እያለ ይደመጣል። ብቻ ሁሉም ያሳዝናሉ፣ በጉልበታቸው እየተመኩ ነው፣ በዚህ አስከፊ ወቅት እንኳ የሚያስቡት ሥልጣናቸውን ነው።

ቀደም ሲል መጋቢት 19 ቀን 2012 ዓ.ም. በአስነበብነው ኢትዮጵያችን ቅጽ 4 ቁጥር 4 (http://www.ethiopiachen.org/images/pdf/Eth_Vol4/140712_1H1H_Ethiopiachin_Vol_4__No_4.pdf) "ዐባይ ለኢትዮጵያችን" እትማችን የዐባይን ግድብ ስኬታማነት መንግሥትም ሆነ የፖለቲካ ድርጅቶች ለፖለቲካ ጠቀሜታ ለማዋል ከመሽቀዳደም ይልቅ በግብፅ በኩል የሚሞከረውን ትንኮሳ ለመከላከልና ለመመከት ሕዝብን ማስተባበር ተገቢ መሆኑን ብናስገነዝብም የዐባይ ጉዳይ በእንጥልጥል እያለ ኮረና ቫይረስ ወረርሽኝ በዓለም ተከሰተ፤ የሕዝባችንን ስሜትም እጅጉን ተቆጣጠረው።

ግብፅ ዐባይን በብቸኝነት የመጠቀም ታሪክ ሳቢያ በኢትዮጵያ ላይ ስታደርግ የነበረው ሤራ ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ ግልጽ ነው። በአሁኑ ወቅትም ግድቡ ላይ ያነጣጠሩ ፖለቲካዊ፣ ዲፕሎማሲያዊና ወታደራዊ ተጽዕኖዎች አጠንክራ ቀጥላለች። ይህ የሚታወቅም፣ የሚጠበቅም ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት ለዚህ ብሔራዊ ጉዳይ ያለው ዝግጁነትና በሀገር ውስጥም በውጭም ያለውን ሕዝብ ማስተባበርና መምራት ጊዜ የማይሰጥ አሳሳቢ ጉዳይ ነው። በአሁኑ ጊዜ የግብፅ ዘመቻ እንደ ጥንቱ ወራሪዎች ኢትዮጵያችንን መያዝ፣ መግዛት አይደለም። የግብፅ ዋና ዓላማ በግድቡ ላይ የደህንነት ስጋት መፍጠር፤ ካልሆነም ጥቃት መሠንዘር ነው። ይህም በአየር፣ በወታደራዊ ኮማንዶ ወይም በሰርጎ ገብ ኃይሎች በመጠቀም፤ ከተቻለም ከምድርም ሆነ ከባህር የሚደረጉ የሚሳኤል ጥቃቶችን በግድቡ ላይ ማድረስ ነው። ግብፅ ያደረገችውና እያደረገች ያለው የአሜሪካን ዳኝነትን መጠየቅ፣ የጦር መሣሪያ ማሻሻሉም፣ ወታደር ማዘጋጀቱም፣ የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት አቤት የማለት ጥድፊያውና ሌላም የግድቡን በሐምሌ ወር መሞላትን ተከትሎ የሚደረግ ዘመቻ ነው። በተያያዥነት ግድቡ በውሃ ሳይሞላ ወይ ማስቆም ወይ ማሰናከል ነው የግብፅ ቀዳሚ ዓላማ። በቢሊዮን ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ በውሃ የሞላ ግድብ ቢፈርስ የታች ተፋሳሽ ሀገሮች ላይ የሚያደርሰው አደጋ ይታወቃልና ከሙሌት ጊዜው አስቀድማ ጥቃት ለመሰንዘር እየተንደረደረች መሆኑ ይገመታል። በመሆኑም አሁን ጊዜው የመወቃቀሻና የመወጋገዣ ሳይሆን እንደ ዐድዋ፣ ማይጨው፣ ሶማሊያው እና ባድመው ጦርነት ብሔራዊ አንድነትን አጠናክሮ የግድቡን ደህንነት መጠበቅ፣ የታቀደው የሐምሌ ሙሌት እንዲሳካ ማገዝ፣ የሚያስፈልገውን የቁሳቁስ ሆነ የገንዘብ ድጋፍ ማስተባበር ይጠይቃል። የጠ/ሚር ዶክተር ዐቢይ መንግሥት ይንን ማስተባበርና መምራት ታሪካዊ ኃላፊነት ይጠበቅበታል። ግብፅ የኮቪድ 19 ወረርሽኝን እንደ ማጥቂያ ልትጠቀምበት ትከጅላለችና ይህ ስለ ምርጫ፣ ስለ ሕገ መንግሥት፣ ስለ ሽግግር መንግሥት ወዘተ. መነታረኪያ ጊዜ አይደለምና ቀዳሚ ተግባራችን ወረርሽኙ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ መረባረብና የዐባይን ህዳሴ ግድብ ሙሌት ስኬታማ ለማድረግ ብሔራዊ ጥቅማችን ላይ የምናተኩርበት ወቅት መሆን ይገባዋል።

ኮረና ቫይረስ በጦርነት ክተት! በዲፕሎማሲው መስክ ግንኙነት አቋርጠናል፣ በብሔራዊ ስሜት ዘራፍ! . . . ብለን የማንወጣው ወረርሽኝ እምነት ላለን እንደየእምነታችን "አቤቱ አድነን ከመዓቱ" የምንልበት አንድ ተስፋ ብቻ ከፊታችን ተደቅኗል። ከዚህ መንፈሳዊ ተስፋ ባሻገር ሊደርስ የሚችለውን አደጋ ለመከላከል፣ መጠለያ ለሌላቸው፣ የሚበሉት በቀን ተባራሪ ለሆኑ፣ በሥራ እንቅስቃሴ መቆም እጃቸው ለልመና የተዘረጋ፣ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል ላላገኙ ሚዳረስበትን፣ ውሃና ሳሙና የሚገኝበትን ሌላም ሌላ ሀገራዊ ጉዳይ ላይ መረባረብ ሲገባን፣ እየጮህንለት ነው የምንለው ሕዝባችን በዚህ ወረርሽኝ ያለበትን ጭንቀት ከተረዳን ልናግዝ እምንችለው ላይ መረባረብ ሲገባ ስለ ምርጫና ሽግግር መንግስት ንትርክ ውስጥ የምንገባበት ወቅት አይደለም።

በአጠቃላይ የዓለምን፤ በተናጠል የሀገራችንን ነባራዊ ሁኔታ ከቃኘን እውን መንግሥትና ፖለቲከኞች አጀንዳቸው እንዴት ሕዝባችንን ከዚህ ወረርሽኝ እንከላከል? ቢሆን በተገባ ነበር። ጋዜጠኞችና የመገናኛ አውታሮች የአየር ሰዓታቸውን በወረርሽኙ ላይ ባዋሉት ነበር። ትበለው አትበለው ባናውቅም "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል" እንዳለችው እንሰሳ ለምን ይኮናል። "ባልበላው ጭሬ ላፍሰው" እንዳለችው ማስካካቱ ቀዝቀዝ ቢል ይመረጣል።

ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ የኢሕአዴግ ሕገ መንግሥት ላይ ያለንን አቋም ገና ጠ/ሚ ር ዶክተር ዐቢይ ሥልጣን እንደጨበጡ ኢትዮጵያችን ቅጽ 3 ቁጥር 4 "የኢሕአዴግ ሕገ መንግሥት ጠንቅ ለአንድነት" በሚል ርዕስ አስነብበናልና አንደግመውም። (http://www.ethiopiachen.org/images/pdf/Eth_Vol3/071411_1H1H_Ethiopiachin_Vol_3_No_4.pdf) ይህን ሕገ መንግሥት የሚቃወም ፖለቲካ ድርጅት ሕገ መንግሥቱን እየጠቀሱ ሲከራከሩ አጀብ! ያሰኛል። በሌላ በኩል ያለውን አገዛዝ ጨምሮ ሕገ መንግሥቱ አይነካብን ባዮች ሕገ መንግሥቱን ለማስፈራሪያ መጠቀማችሁ ጥንትም የመለስ ዜናዊን "ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ሊንዱ" ፉከራዎች ከመድገም ሌላ የጨመራችሁት እንደሌለ ብትረዱት በተገባ። ጆሯችንን ማመን ካላቃተን በቀር 27 ዓመት የገዛው ኢሕአዴግ ሕገ መንግሥትና ሥርዓት ዛሬም እንደቀጠለ ጠ/ሚሩ በሚያዝያ 29 ቀን 2012 ዓ.ም. ንግግራቸው አስረግጠው ነግረውናል። ከነገረኝ የደገመኝ አይሁንና በተለይ ለደጋፊዎቻቸውና ለአድናቂዎቻቸው ንግግራቸውን ደግመን እናስቀምጥ፤ ". . .***በዚህ አጋጣሚ በግልጽ መታወቅ ያለበት ነገር አለ። በኢትዮጵያ ያለው ለውጥ ሪፎርም (ጥገናዊ) እንጂ አብዮት አይደለም። ሕገ መንግሥት ቀይረን አዲስ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት እየገነባን አይደለም። ገዥው ፓርቲም ታድሶና የሕዝብ ተቀባይነትም ጨምሮ ገና ጀምበሩ እየወጣ ያለ አዲስ ጉልበትና አቅም ያለው በቀጣዩም ምርጫ እጅግ ሰፊ የማሸነፍ ዕድል ያለው ፓርቲ እንጂ ተሰናባችና ጀምበሩ ያዘቀዘቀ ስብስብ አይደለም። . . .***" ሥርዝ የተጨመረበት። የአማርኛ ትርጉም ለሚያስፈልጋችሁ፤ ጠ/ሚሩ ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም "እንግዲህ እረፉት እኛ የኢሕአዴግ፣ የመለስ ግርፎች ይህችን ሀገር ዛሬም ሆነ ነገ በዘርና በቋንቋ ከፋፍለን እንገዛለን፣ ምርጫን እንደ ጥንቱ መቶ በመቶ እናሸንፋለን፣ የመደመር ፍልስፍናዬ አልፋና ኦሜጋ ነው" መልዕክታቸው ከማን ነቅንቀን ስሜታቸው ጋር አስደምጠውናል።

ትግላችን ከህወሓት/ኢሕአዴግ የሆነ፣ ለሥርዓት ለውጥ ስንል ለሕገ መንግሥቱ መናድ መሆኑን ከተቀበልን የዛሬ 20 ዓመት ገደማ በተጀመረው የወያኔ የይስሙላ ምርጫ አጃቢና ከሃዲ በመሆን የአገዛዙን እድሜ አራዝመው ዛሬም ይህንኑ ሊደግሙ የሚራወጡ ፖለቲከኞች አየሩን ሲሞሉት እየታዘብን ነው። ትላንት በዘንድሮው ምርጫ ትንሽ ወንበር ይዘን፣ በሚቀጥለው ሌላ ጨምረን እያሉ ወያኔን 27 ዓመት ያገዙት አንዳንድ ተቃዋሚዎች ትላንት ሕዝብ ላይ እንዳሾፉ ዛሬም ሲመጻደቁ አለማፈራቸው። በ1997 ዓ.ም. ምርጫ ያበቃለትን ኢሕአዴግ እውን ማነው ፓርላማ ዘሎ እድሜ ያስቀጠለው? ማነውስ "የሙት ቀን" አድማን ሠርዞ ለመለስ እፎይታ፣ ለሕዝባችን ያላባራ እሮሮ የለገሰው? የእኛ ፖለቲከኞች የቅርብ ጊዜ ታሪክ ይህ ነው።

ጠ/ሚ ር ዐቢይ አሕመድ ገና ከጅምሩ ኢትዮጵያን ለማፈራረስና ለማዳከም በርካታ ተጠቃሽ ማህደር ያላቸውን ኢሳያስ አፈወርቂን ይዘው ጨፍረዋልና "እኔስ በኢትዮጵያ ህልውና ላይ ካነጣጠረ አሸባሪ ፖለቲከኛ ብገናኝ፣ ከህወሓት ብፋቀር ችግሩ ምንድን ነው?" አባባልና ሰይጣናዊ ምርጫ፤ ጥፋት ፉክክር እንዳልሆነ አለመረዳት ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ ድንቁርና ነው። የመንግሥቱ ኃ/ማርያምን በሙቶ ሺህ ግድያ ያልጠበቀ "ኃይሌ ማረኝ" ቢል የፖለቲካ ሀሁ አልገባውምና አይፈረድም። የወያኔን ሀገር ብተና የተረዳ ትውልድ "መንጌ፣ መንጌ" ቢል የሕዝብ ስቃይና እየዩ በሀገር ከለላ እንዴት እንደጠዘ አስረጅ አላገኙምና አይታዘንባቸውም።

በሀገራችን በለውጥ ስም ብቅ ያሉት ጠ/ሚ ር ዶር ዐቢይ አሕመድ በሁለት ዓመት ጉዟቸው አግኝተውት የነበረውን ሕዝባዊ ድጋፍ በጥፋታቸው አጥተውታል። ሕዝባችን ከወሬና ፉከራ በላይ ተግባር እጅጉን አስተምሮታል። የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ እያውለበለበ፣ ሀገሬ ኢትዮጵያን እያዘመረ ልጆቹን ቀብሮ ከፈረጠጠው ደርግ ብዙ ተምሯል። ደርግ ለዘረኛና ለከፋፋይ አገዛዝ ሀገሪቷን አመቻችቶ ሀገርና ሕዝብ ህልውና ላይ ያነጣጠረው የ27 ዓመት አገዛዝ በለውጥ ስም "ስንኖር

ኢትዮጵያ ስንሞት ደግሞ ኢትዮጵያውያን” ቢባልለትም እያደር ተግባር አዬዬ አሰኝቶታል። ሕዝብን እያቀፉ ማስለቀስ፣ ልጆቹን እየገደሉ ለቅሶ መድረስ፣ ነዋሪን እያፈናቀሉ አልሰማሁም፣ “አዲስ አበባ ቤቴ” ሲጨፈር ጦርነት አውጃለሁ፣ ኸረ ፍጅት በዛ ሲባል ዘር ቆጠራ፣ የደምቢዶሎ ታጋቾችን ጉዳይ ተባብሮ ማፈን፣ ኸረ ቆራጥ አቋም ይወሰድ ሲባል ከለላ መስጠት፣ ጥንታዊ መለያችንን አንበሳ በፒኮክ የመተካት ደባ፣ ሌላም ሌላ የየዕለት ተግባራቸው እየሆነ የመጣው የዶር ዐቢይ አገዛዝ እንዴት አድርጎ በምርጫ ስም አገዛዙን እንደሚያራዝም ያለ የሌለ አቅሙን በመጠቀም ይኳትን እንደነበር የቅርብ ወራት ሁኔታ ነበር። ዛሬ ኮረና ቫይረስ መጣና ሳያስቡት እቅዳቸው ከሸፈ፣ ምርጫው ተራዘመ እንጂ የምርጫው ውጤት ለዘረኛ የፖለቲካ ድርጅቶች ፍጥጫ፣ ለህወሓት ግንጠላ፣ ለብልጽግና መደመር፣ ለተፎካካሪዎች ጉሮ ወሸባዬ እየአመቻቹ የተጓዙበት ሂደት ነበር።

የሚያዝያ 27 2011 ዓ.ም. እትማችን ኢትዮጵያችን ቅጽ 3 ቁጥር 6 “በምርጫ ስም ኢትዮጵያችን አትከፋፈልም” እትማችን ምርጫው ወዴት እያመራ እንደሆነ አስቀድመን ጠቁመናል። (http://www.ethiopiachen.org/images/pdf/Eth_Vol3/072711_1H1H_Ethiopiachin_Vol_3_No_6.pdf) ምርጫው ይካሄድ እንጂ ክልላችንን የመያዝ ዕድላችን በእጃችን ነው ያሉ ፖለቲከኞች የኮቪድ 19 ሕዝብ ላይ የደቀነው አስከፊ አደጋ ሳያሳስባቸው ከመስከረም 30, 2013 ዓ.ም. በኋላ የመንግሥት አለመኖርን ሊነግሩን፣ ጉድ እንደሚፈላ ሊያስፈራሩን ሲሞክሩ ይደመጣሉ። እነ መለስ ዜናዊ በተለያየ መልኩ ለሀገር አፍራሽነት ያመች ዘንድ ቆላልፈው ያስቀመጡት ሕገ መንግሥት ኖረ አልኖረ ሀገርና ሕዝብ ዘላለማዊነቱን ቢረዱት መልካም ነው። ኮቪድ 19 ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት እንዴት መቀነስ እንደምንችል ሁላችንም በጋራ መረባረብ ሲገባን ስለ መበታተን ሲደሰኮር፣ የሀገርን መንግሥት አልባነት ሲመኙ፣ ግርግር ናፋቂ ሲኮን፣ ኮቪድ 19 ሀገር ለመበተኛ ሲመኙት እንደተለመደው ድብቅ ተልዕኮአቸው እያመለጠ አደባባይ ወጣ እንጂ ያልተጠበቀ ጉዳይ እየነገሩን እንዳልሆነ ቢረዱት መልካም ነው።

የሽግግር መንግሥት ፈላጊ የፖለቲካ ድርጅት በሁለት ቢላ ሊበላ አይነሳም። የሽግግር መንግሥትን አስፈላጊነት እጅጉን እየሰበኩ ከሕዝብ ጋር ሁኖ መታገል ማታገል። የሽግግር መንግሥትን መሪ መፈክር በማድረግ ኃይልና ሥልጣን ከሕዝብ ለሕዝብ ይመነጭ ዘንድ ቁርጥና ውስኪ ሳይጎመጁ መታገል! መስዋዕትነቱ ቢቀር እንኳ እሥርና ክትትል ሳይፈሩ ትግልን ዓላማ ማድረግ። የምርጫ ድራማን “ባጣ ቆዩኝ” ዓይነት ብልጣብልጥነት እንደአማራጭ መጠቀም እጅጉን የተበላ አካሄድ ነው። ለለውጥ አራማጁ ተንበርክኮና አደብ ገዝቶ የወር ደሞዝ የሚያስከፍል፣ መኪና የሚያሰጥ፣ ኮንዶሚንየም የሚያስገኝ፣ በፓርላማ ትንሽ ወንበር አስገኝቶ ኮትና ከረባት የሚያስለብስ ገጸ በረከት ከኢሕአዴግ/ብልጽግና ፓርቲ በማግኘት በሚቀጥለው ምርጫ ቀስ በቀስ ለሥልጣን እንበቃለን እያሉ ፖለቲካን ኑሮ ማድረግ፤ እጅግ አሳዛኝና አሳፋሪ የቅሌት ድግምግሞሽ ያሰኛል። አሁን በሕዝባችንና በሁላችንም ላይ ከፊት ለፊታችን የተደቀነ አስከፊ ወረርሽኝ ሀገራችንን ወዴት እንደሚወስዳት ስናስበው በስጋትና በድንጋጤ የማይዋጥ ዜጋ አረመኔነት ተግባር ነው ቢባል አያስደንቅም። ከመስከረም 30 በኋላ “በሕገ መንግሥቱ መሠረት መንግሥት የለም” ስንል እውን 28 ዓመት የታገልነው በሕገ መንግሥት የገዛንን መንግሥት ነው ወይስ በምርጫ ስም አንዴም ያልተሸነፈን ወንበዴ አገዛዝ? አዲስ አበባ በምርጫ ልታመልጠው ሲሆን በ24 ሰዓት ውስጥ ሕግ የቀየረ የመለስ አገዛዝ ውጤት እኮነው ዛሬም ያለው። ኢሕአዴግን የሚያነቃንቅ ሁኔታ ሲመጣ “ኢንተርሃሞይ፣ ቢጫ አብዮት” እያለ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚያውጅ አገዛዝ ተቀጥላ የሰሞኑ ዛቻ፣ እርምጃ እወስዳለሁ፣ ሽግግር መንግሥት እንዴት ተነስቶ አካሄድ እውነት ኮቪድ 19ን ለፖለቲካ ፍጆታ ሊጠቀሙ ከሚፈልጉ ምን ይለየዋል? ትላንት 86 ዜጎቻችን በአንድ አሽባሪ ትዕዛዝ ማለቃቸውን ምክንያት

አድርጎ መንግሥት እርምጃ እንዲወስድ ኡ..ኡ.. ሲባል ያሾፈ አገዛዝ ከበስተጀርባ ድብቅ መልዕክት ከሌለ በቀር ስለ ሽግግር መንግሥት ውይይት ተካሄደ አልተካሄደ ምን ያስጨንቀዋል?

***"ሥልጣን የሚፈልጉ የፖለቲካ ኃይሎች የሀሳብ ክርክሮቻቸው ወጣቱንና እናቶችን በማይጎዳ መልኩ እንዲያደርጉት ይመከራል። ፖለቲከኞች ሥልጣን እንዲይዙ ወጣቶች ማለቅ፣ እናቶች ማልቀስ፣ ቤቶች መፍረስ፣ ሕዝቦች መፈናቀል የለባቸውም። የኢትዮጵያውያን ጫንቃ ይህንን ከሚሸከምበት ደረጃ አልፏል።"*** ይሉናል ጠ/ሚር ዶር ዐቢይ በሚያዝያ 29ኙ ንግግራቸው። እውን ለ28 ዓመት በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶችን በየእሥርቤቱ እያጎረ፣ እያሰቃየ፣ እየገረፈ፣ እየገደለ፣ ለስደት እየዳረገ የተጓዘ የኢሕአዴግ ሥርዓት አይደል እንዴ ዛሬም ትኩረቱ የወጣቱ እንቅስቃሴ ላይ በማድረግ የሚያሰቃየው? ከኖሩበት ቀዬ እያፈናቀለ እናቶችን የሚያስለቅስ አገዛዝ፣ ቤት የሚያፈርስ ፌደራል፣ ሕጻናትን የሚያስርብ አገዛዝ፣ አስገድሎ ለቅሶ ሚደርስ ከንቲባ፣ እሽሩሩ እያሉ ምናለ በቁስላችን ላይ እንጨት ባይሰነቅሩ።

ዛሬ በሀገራችን አሳሳቢው ጉዳይ በዓለም ደረጃ የተከሰተው ወረርሽኝ ነው። ማንም አእምሮ ያለው ዜጋ በግልም ሆነ በቡድን ይህን አስከፊ መቅሰፍት ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ የአቅምን መረባረብ አስፈላጊ ነው እንላለን። ሀገራችን የጠ/ሚር ዶር ዐቢይ መንግሥት ሥልጣን ከያዘበት ማግስት አንስቶ በየአካባቢው በአለው አለመረጋጋት ከጊዜ ወደ ጊዜ የኑሮ ውድነት እያሻቀበ ዛሬ ደግሞ እጅግ በሚዘገንንና አቅምን በሚፈታተን ሁኔታ ላይ ሀገር ተዘፍቃለች። ለወረርሽኙ መከላከያ በተዘፈቅንበት ብድር አሁንም በልመናና በብድር ከመዘፈቅ ሌላ አማራጭ የለንም። ዛሬ መሽቶ እስኪነጋ አይደለም በየደቂቃው "ምን ይሰማ ይሆን?" የምንልበት ሥጋትና ውጥረት ላይ ሌላ መከራ፣ ሌላ አጀንዳ ስንፈለፍል ያሳፍራል። የመንግሥትም አምባገነንነት እንደተጠበቀ፣ የተፎካካሪ ፓርቲዎችም ፖለቲከኛነት እንደተከበረ፣ የዘረኞችም መንግሥት ምሥረታ እንደአስቃገር ለዚህ ምስኪን ሕዝባችን ስንል ወረርሽኙ ላይ እናተኩር። ለሕዝብ ነው የምንሞግተው፣ የምናስበው ከሆነማ የወረርሽኙን ጭንቀት እንካፈለው። ፈጣሪ ድንገት ለመጣው ወረርሽኝ መፍትሄ አስገኝቶ ይማረንና መባላቱን እንደርስበታለንና እስቲ ለደቂቃ ዝም! እንበል።

ወያኔ ሰራሹ የኢሕአዴግ ሕገ መንግሥት የመጽሐፍ ቅዱስ/የቁራን ቃል አይደለምና እንዲህ ዓይነት ተፈጥሮአዊ አደጋ በምርጫ ወቅት በሚከሰትበት ወቅት ያለው አገዛዝ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሀገሪቱን እያስተዳደረ ምርጫውን የማራዘም ኃላፊነት እንዳለው በማስተካከል ፖለቲካዊ ውሳኔ መስጠት ይጠበቃል። አዎ! ፍርሃቱ ይህ ሀገር በታኝ ሕገ መንግሥት በዚህ ሁኔታ ከተነካ በቀጣይነት ሌሎች አንቀጾች ወደፊት እንዲሻሻሉ ጥያቄ ያስነሳልና መንግሥት ከዚህ ስጋት ለማምለጥ ያሰበው ጉልበት የመጠቀም አዝማሚያ አዋጭ እንዳልሆነ እንጠቁማለን።

በመጨረሻም ለሀገርና ለሕዝብ ሲባል መንግሥትም ሆነ ተፎካካሪ ፓርቲዎች በአንድ በኩል በየቀኑ ቁጥሩ እየጨመረ የመጣውን ኮቪድ 19 ስጋት ለመከላከል በጋራ መረባረብ፤ በሌላ በኩል ከግብፅ ሊሰነዘር የሚሞከር ትንኮሳን በማያዳግም መልኩ ለመመከት ነቅተን መጠበቅ ይገባናል። ወረርሽኙ የሚወስድብን እርምጃ ይበቃልና አንፎክር። በየቤቱ የከለለን ኮቪድ 19 ይወገድልንና እስቲ በሠፊው ለመካለል ያብቃን። እስቲ ኮረና ቫይረስን ተሻግረን እናምልጠውና ለሽግግር መንግሥት ያብቃን። እስቲ የኮቪድ 19ን ገዳይነት እናምልጥና ብልጽግናን ለመምረጥ ያብቃን።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!
ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይባርክ!!!
የኮረና ቫይረስ ወረርሽኝ ከዓለማችን ይርቅልን ዘንድ ፈጣሪ ይርዳን!!!

**አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ**
**ግንቦት** 2 **ቀን** 2012 **ዓ.ም**. (May 11, 2020)

<u>ማሳሰቢያ ፡</u>

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» «***ኢትዮጵያችን***» ልሳን በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org , www.ethiopiachen.com
ምሥለ ገጽ ፡ 1H1H Ethiopiachin